"ሞጣ ቀራንዮ ምነው አይታረስ
በሬሳ ላይ መጣሁ ከዚያ እስከዚህ ድረስ" ሚኪ

ይህን አባባል በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቅኔ የተማሩ ሁሉ ያስታውሱታል። "ሞጣ ቀራንዮ" - አንድ ደብተራ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ምድር ተከስቶ የነበረውን አስከፊ የጦርነት የገለጹባት አጭር -ነገር ግን ሠፊ ትንተና ያዘለች ሰምና ወርቅ (wax and gold) ቅኔ ነች። በሬ የለም - አራሽ የለም -መሬቱን ሬሳ ሞልቶታል። የሰው ልጅ ጉልበትና ዓዕምሮ ለልማት ከመዋል ይልቅ የሰው ልጆች ህይወት በከንቱ ሲጠፋ ቢያዝኑ ጊዜ ነው ደብተራው "በሬ ሳላይ መጣሁ" ያሉት። "በሬ ሳላይ" የጎብሩው ቃል ሲሆን "በሬ ሳላይ" ማለትም ምንም በሬ አላየሁም፣ አራሽ የለም - የቅኔው ሰም አገላላጽ ነው (wax – the apparent figurative meaning of the word)። "በሬሳ ላላይ መጣሁ" ማለትም በበድኖች ላይ፣ በሙታን ላይ ተራምጄ መጣሁ - አሳዛኙ የቅኔው የወርቅ አገላለጽ ምሥጢር ነው (gold – hidden and actual significance - philosophical foundation of Ethiopian hermeneutics)

የሠሜን ኢትዮጵያ መሬቶች የጠላቶች መቀበርያ ሆነዋል። መቅደላ፣ ጉንደት፣ ጎራ፣ ኩፊት፣ ዶጋሊ፣ ጎንደር፣ ዋግራ፣ ጋላባት፣ ኮኣቲት፣ ሰናፌ፣ አምባላጌ፣ መቀሌና አድዋ ላይ ይህችን አምሳለ ገነት ሊወስድ የመጣ ጠላት ሁሉ ተቀብሮባታል። በእርግጥ የሰሜኑ የሃገራችን ክፍሎች በወገን ደም ጨቅይተዋል። በጥቂት ግለሰቦች ግትርነት ሳብያ የደሃ ደም ምድሩን አለበሰ።

የሰሜኑ እርስ በእርስ ጦርነት ረዥም እድሜ ያስቆጠረ የግፈኞች የሴራ ውጤት ነው። ሴራው መግደልና መሞትን ከመኖርና ከማምረት ይልቅ አድናቆት ይቸረዋል። ሴራው ውጊያና ድፍረት የሰው ልጅ መሠረታዊ ጸጋ አድርጎ ስለሚቆጥር ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱትን ሁሉ በውጊያው እንዲሰለፉ ቀቢጸ ተስፋ ይሞላቸዋል። አንድ ምሁር እንዳሉት በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የወንድነት ጾታ የሚለካው በማምረት አቅሙ ሳይሆን በውጊያ ችሎታውና ድፍረቱ ብቻ ነው። መሰሪዎች ይህን የዓላማቸው ማስፈጸምያ ያደርጉታል። ጥቂት ሰዎች ለራሳቸው ዝናና ሃብት የደሆች ልጆችን ያስጨርሳሉ።

ከሰሜኑ ወገናችን ድንቅ ባህላዊ ጨዋታዎች ጋር አብረን የተወዛወዝን አንጻራዊ ሠላም ባለበት የተቀረው የኢትዮጵያ ምድሮች እንዲሁም በውጭ የምንገኝ ሁሉ አስከፊ የሆነው የእርስ በእርሱን ጦርነት ከመታዘብ ውጭ ጦርነቱን ለማስቆም አንዳች መፈየድ አልቻልንም። የገንዘብ መዋጮአችን ያችን በለጋ እድሜዋ እግሯ ለተቆረጠውን ሕጻን ምርኩዝ አይሆንም። ርዳታችን ገና በወጣትነቱ ድፍት ያለውን ኮፈሌ ህይወት አይመልስም። ርጥባናችን ምንም በማያውቁት ነገር ተገድለው በየሜዳው የተጣሉትን ከብቶች ነፍስ ዳግም አይዘራም። እንደ እውነቱ ከሆነ በየፊናችን የምንለግሰው ገንዘብ የወደሙ ቤቶችን ለመጠገን፣ የተቃጠሉ ቤተ እምነቶችን ዳግም ለመመልሰ፣ የፈራረሱ ድልድዮችን፣ ትምህርት ቤቶችን፣ ወፍጮ ቤቶችን፣ መንገዶችን፣ ወዘተ፣ እንደገና በሥራ ላይ ለማዋል በቂ አይደሉም። ብቻ ያለውን የወረወረ ቸር ነውና ልገሳው ለወገን አፋጣኝ ሰብዓዊ ርዳታ ሆኗል። ካላቸው ላይ ቆንጥረውም ሆነ ከጉድለታቸው መዘው የሚረዱ ወገኖችን ሁሉ እግዚአብሄር ይባርካቸዋል። አሁንም እግዚአብሄር ይርዳን፣ ችግሩ ብርቱ ነውና ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ካለን ቁሳቁሶችና እህልም ጭምር ቀንሰን ለማካፈል እንትጋ።

ሁሉም ነገር ያሳዝናል። አሁን ባለንበት ክፍለ ዘመን በሰሜኑ የሃገራችን ክፍሎች አሁንም በሬሳ ላይ መራመድ አልቀረም። አሁንም በሬዎች የሉም፣ ምድሪቱ ከምዕራቡ ዓለም በተገዙ አውዳሚ የጦር መሳርያዎች እየነደደች ነው። በየመንደሩ የሚደፈሩና የሚጠቁ እናቶችንና እህቶችን ዜና እየሰሙ መብላት መጠጣቱም እርም ሆኖብናል። ዜናዎቹ ለተጎዱ ወገኖችም ሆነ በሰቀቀን ለሚሰሙትም ታላቅ የሥነ ልቦና ችግር ነው። ቁም ስቃይ የሚያዩ የየቤተ ክርስትያናቱና ገዳማት አባት እናቶች ደም እንባ እያለቀሱ መብላት መጠጣቱስ ሰውነት ይሆናልንስ? ጥንታዊ ቅርሶች ሲወድሙ በዓይናችን ማየቱ - በእርግጥ ይህስ ማንን ያስደስታል?

ወገኖቼ! በሰሜኑ የሃገራችን ክፍሎች ያሉ በርካታ መንደሮች ወድመዋል። የህብረተሰቡ ጎበዞችና ጎልማሶች በጦርነት ተሰውተዋል። ትምህርት ቤቶች ተዘግተው ህጻናትና ወጣት ተማሪዎች ተበትነዋል፣ ተሰደዋል። እርሻ የለም - በሬውም አራሹም ሞተዋል፣ ሴቶች ካለ ርህራሄ ይደፈራሉ፣ ቅርሶች ተዘርፈዋል፣ ቤት እምነቶች ነደዋል፣ አቅም የሌላቸው ቀዬአቸውን እየለቀቁ ተሰደዋል። አቤቱ እግዚአብሄት – እንዲህ ያለውን የሰቆቃ ዜና እንዳንሰማ ምን እናድርግ? ምን ይሆን መፍትሄው?ገንዘብ ማዋጣቱም፣ ቁሳቁሶችን ማካፈሉም ዘለቄታዊ መፍትሄ አይሆንምና፣ ፈጣሪ ሆይ ምን ትለናለህ?

ወገኖቼ! ማቅ ለብሰን እያነባን እንጸልይ። ለይስሙላ ሳይሆን ይህ ሁሉ መከራ እኔና ዘመዶቼ ላይስ ቢሆን የደረሰው ብለን – በተሰበረ ልብ ወደ እግዚአብሄር እንጩህ። እግዚአብሄር ደንዳና ልባችንን – ንዋይ ንዋይ የሚሸተውን እዕምሯችንን – እንብላ እንብላ የሚልውን ስጋችንን - ፍላጎትና መጠን ስለሚያውቅ ነው ጸሎታችንን የማይሰማው። ቤተ ክርስትያን ለይስሙላ መመላለሱን አቁመን – እርስ በእርስ ይቅርታ እንጠያየቅና - እርሱ ፈጣሪን እንደ ዳዊት በተሰበረ ልብ እንቅረብ። በጸሎት መርሃ ግብሮች ታድመን ሳለን ልባችን እሌላ ቦታ መሰደዱን እርሱ አምላክ ያውቃልና ጸሎት በሚመስል ጫጫታ አንሸንግለው፣ ይልቁንም እየግዚአብሄርን ረደኤትና ኃይል በላያችን ያድር ዘንድ ራሳችንን እናዋርድ።

አቤቱ – እግዚአብሄር፣ የሃጢዓታችን ክፉ ሽታ ወደ ሰማይ እንዳይወጣ በቃልህ ማዕዛ ጣፋጭ አግድረግን፣ እውነተኞችና ደጋግ አድርገን። እባክህ አምላኬ ይቅር በለን፣ አገራችንንም ስቃዩን በቃሽ በላት። እባክህ አምላኬ ርህራሄህ ከላይ ከማደርያህ ይውረድ፣ አምላኬ ሆይ፣ ይቅርታህን አልብሰን፣ ወገኔን ከክፋት ሰውረው። ጌታ ሆይ - እበላለሁ እጠ|ጣለሁ፣ በውድ ዋጋ የተገዙ ልብሶች እለብሳለሁ፣ ምን ያደርጋል፣ ውስጤ ግን አረካችም። እባክህ እግዚአብሄር ነፍሴህ ሃሴት አልብሳት። እባክህ አምላኬ ቃል ለገባህላት፣ ዝንተ ዓለም ስምህን ላወደሰችው፣ ብርቱዋ ኢትዮጵያ ሰላም አስፍንላት። አሜን።